# የሴቶች ቀን ዝክር



ከገነት ድንቅነህ (ኖርዌይ ኦስሎ)

በተለያዩ ሀገሮች ያለው የባህል፣የሀይማኖት እና የፖለቲካ ልዩ የሆነ አመለካከት በሴቶች ላይ እንዲሁ የተለያየ ከባድ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡በሁሉ የህይወት አቅጣጫ የሴቶች መብት በእኩልነት ያለመከበሩ ጉዳይ ያስቆጣቸው ሴቶች ለነጻነታቸው እና ለሰብዐዊ መብቶች እኩልነት ክብር እንዲሁም የጭቆናው ቀንበር ያጎበጣቸውን ቀና አድርጎ በእኩልነት ለማኖር ባደረጉት ያልተቋረጠ እና ያላሰለሰ ትግል በዓመት አንድ ቀን በመላው አለም የሴቶች ቀን እንዲከበር ተወስኗል፡፡ ቢሆንም በተለይ ኋላቀር በሆኑ ሀገሮች ነዋሪ የሆኑቱ ላይ እስካሁን ሊቀረፍ ያልቻለው የሴት የበታችነት ጉዳይ ኢትዮጵያን ጨምሮ በጉልህ የሚታይ ችግር ነው፡፡ ለሀገር ዳር ድንበር መጠበቅ በእኩልነት የትኛውም የተፈጥሮም ሆነ ከሌላ አቅጣጫ የሚመጣ ተጽዕኖ ሳይገድባቸው ከወንድ ታጋዮች ጋር በመሰለፍ ወጣት ሴቶች መሳሪያ በማንገብ እናቶች ደግሞ በአርበኛ ወኔ ስንቅ በመሰነቅ ለሀገራቸው በእኩልነት ለህይወታቸው ሳይሳሱ የከፈሉት መስዋእትነት ቀላል የሚባል ሳይሆን ሁልጊዜም በአህጉሪቷ ላይ ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯን በማስጠበቅ ረገድ የአፍሪቃ ምሳሌ እንድትሆን ቀላል ያልሆነ መስዋዕትነት ከፍለው አልፈዋል፡፡

በዚሁ በየዓመቱ በሚከበረው የሴቶች ቀን ከህዝብ ጋር ተቀላቅለው በአሉን መዘከር እና ማክበር ያልቻሉትን ለሰላም ለነጻነት ለፍትህ እና ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ሲታገሉ በአምባገነኑ ገዢ ቡድን ወያኔ ታላቅ የሆነ ኢሰብአዊ ድርጊት ተፈጽሞባቸው በሀገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቆጠር ለእስር የተዳረጉትን ከፍተኛ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ፣ አባላቶች እና ደጋፊዎች ፍትህ ተነፍገው የት እንዳሉ እንኳን ሳይታወቅ ደብዛቸው እና ድምጻቸው የጠፋውን የፖለቲካ እስረኞች ልናስባቸውና ልንዘክራቸው እንወዳለን፡፡

ምንም እንኳን በወያኔ አንቀጽ 35 ላይ ስለ ሴቶች እኩልነት እና መብት የተቀመጠ ቃል ቢገኝም ሴት እህቶቻችን በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ድረስ ያልታየ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት እንግልትና ግፍ እየገጠማቸው ይገኛል፡፡ ገዢው ብድን ህገመንግስት ብሎ ላረቀቀው ህጎቹ ሳይገዛ እና ምንም ተጠያቂነት

ሳይሰማው አላየሁም አልሰማሁም በሚል የተለመደ ዘዬው ከቀን ወደቀን እየጨመረ በመጣው ያደንዛዥ ዕፅ የጫት የአልኮልና የዝሙት ችግሮች በመተብተብ ብዙዎቹን ለእልፈተ ህይወት ያበቃውን አስገድዶ መድፈር ፣ የጠለፋ ጋብቻ እና የጨቅላ ሴት ህጻናቶች ሙሽርነት እንዲሁም ግዳጃዊ የሆነ የዝሙት አዳሪነትን ስምሪት በሀገሪቱ ላይ በይበልጥ እየተዛመተ በመጣበት በዚህ ከባድ ወቅት አንዱም ህግ ተፈጽሚነት ሳያገኝ አመታቶች እየተቆጠሩ ይገኛል።

ከዚህ ጋር የሚታየ እጅግ አስገራሚው ክስተት ደግሞ የ ወያኔ ሴቶች ሊግ ፣ የሴቶች ፎረም ወያኔ የሚያዘው እና አገዛዙ ያስተባበራቸው በርካታ የሴት ማህበራት ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለወያኔ መንግስት ስርአት ነው። ስርአቱ ደግሞ የመለው ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ እና ይሁንታ ያላገኘ መሆኑ ነው። ነገሩን ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ከመንግስት ድጋፍ ውጪ በራሳቸው ፍቃድና አቅም አንድም የተደራጀ ማህብር የሌላቸው መሆኑ ነው። እርግጥ ነው የሴቶች የፅዋ እና የእድር እንዲሁም የዕቁብ ማህበራት በአገራችን ለቁጥር የሚታክቱ ነው፤ግን እነዚህ ማህበራት የሴቶችን ሁለንተናዊ ችግሮችን የሚቀርፉ አይደለም። ኢትዮጵያት ሴት እህቶቻችን በአካል ፣ በሞራል፣ በስነልቦና የተጎዳውን ማንነታቸውን ይዘው አልፎም ተርፎ የቤተሰብ ጫና እና ሀላፊነት ስለሚሰማቸው ኢኮኖሚ ለደቆሰው ቤተሰብ የእለት ጉርስ ለማቀበል ወርቃማ የወጣትነት ጊዜያቸውን በማርገፍ ከቀያቸው እየተፈናቀሉ በየአረብ ሀገሩ የኮበለሉት እህቶቻችን አንዳዶቹም ሳይቀናቸው ቀርቶ በበረሀ ጉዟአቸው በምድረበዳ ሰጥመው የቀሩት እንዲሁም ረጅሙን ጉዞ ተሻገርኩ ሲሉም በአሰሪዎቻቸው ጭቆና ከፎቅ እየተወረወሩ የፈላ ዘይት እና ውሀ እየተደፋባቸው ተለብልበው የተቃጠሉ፣ በደረሰባቸውም ምሬት እና ስብራት ተስፋ በመቁረጥ ህይወታቸውን ያጠፉትን የኢትዮጵያት ሴት እህቶቻችንን በደል ስናስብ ለዚህ ሁሉ እልቂት እና የትውልድ ጥፋት ያበቃንን አምባገነኑን ገዢ ቡድን ወያኔን እያወገዝን ነው።

በአለማችን ሴቶችን በመዘከር አንድ ላይ በምንሰበሰብበት በዓል ቀን ሁልጊዜም ታሪክ የሚያወሳቸውን የኢትዮጵያን ሉአላዊነት እና አንድነት ለማስጠበቅ ታላቅ በሆነ የሀገር ፍቅር ተጋድሎአቸውን ሲያካሂዱ በወያኔ ግፋዊ አገዛዝ ሰለባ ሆነው ህይወታቸውን ያጡትን እንዲሁም በዚህ ሰአት ያለ ነጻነት በሀገራቸው ላይ የመናገር እና የመጻፍ መብታቸው ተነፍጎ እንደ መጤ በመቆጠር ወደ እስር ቤት የታጎሩትን እህቶቻችን እና እናቶቻችን ለከፈሉት እና እየከፈሉ ላሉት መስዋዕትነት ታሪካዊ የሆነ ዋጋ በመስጠት ጭምር ነው።

ስለዚህም በየትኛውም አለም የሚኖር ለፍትህ እና ለኢትዮጵያ አንድነት እና ሰላም የቆመ ዜጋ ይህን የአለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሲያከብር በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የአለማችን ሴቶች ለቤተሰብ እና ለሀገር የሚከፈል መስወእትነት

ተምሳሌት የሚሆኑትን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ጀግና ሴቶችን እያስታወስን ሊሆን የተገባ ነው። በተጨማሪም ለሀገራችን አንድነት ዕና ሰላም እንዲሁም ለወያኔ ውድቀት የሚደረገውን ተጋድሎ በያለንበት ስፍራ በሁሉም አቅጣጫ እንደግፋለን። ሴት እህቶቻችን የጀመሩት ስላማዊ የሆነ ትግል ግቡን እንዲመታ በኢትዮጵያዊነታችን አብረናቸው እንደምንቆም ቃል እየገባን እና የሴት እህቶቻችን ችግር የሁላችንም እንደሆነ በመቁጠር ለመረዳዳት ብሎም የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ በተጠናከረ ክንድ አብረናቸው እንታገላለን።

የሴት እህቶቻችን የትግል ጥረት ግቡን ያመታል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ።

genet.tesema17@gmail.com